# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

**በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ**

*(ከነሐሴ 28- ጳጉሜ 04/2016 ዓ.ም)*
September 03- 9/2024

**1. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከዓለም ባንክ የ545 ሚሊዮን ዶላር ብድር ማግኘቱን አስታወቀ**

***Reporter;September 8, 2024***

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር በመሆን ለሚያከናውናቸው የመልሶ ግንባታና የአቅም ማሻሻያ ሥራዎች የሚውል 545 ሚሊዮን ዶላር ብድር ከዓለም ባንክ መገኘቱን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ይህንን ያስታወቀው የ2016 ዓ.ም. አፈጻጸምንና በ2017 ዓ.ም. የትኩረት መስኮች፣ እንዲሁም አዲሱን የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻያ አስመልክቶ ነሐሴ 29 ቀን 2016 ዓ.ም. ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ ነው፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/133140/

**2.በአገር ውስጥ የአውሮፕላን መለዋወጫዎችን ለማምረት የሚያስችል ስትራቴጂ እየተዘጋጀ መሆኑ ተገለጸ**

**Reporter; September 8, 2024**

የኢትዮጵያ አቪዬሽን ኢንዱስትሪ በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ብቻ ተከልሎ ከቆየበት፣ ወደ አውሮፕላን መለዋወጫዎች አምራችነት እንዲስፋፋ የሚያስችል የዘርፍ የሽግግር ፕሮግራም ይፋ ተደረገ።

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ተወካዮች፣ ከግብርና ሚኒስቴርና ከትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ደኤታዎች፣ ከግል አቪዬሽን ተቋማትና ከዘርፉ ባለሙያዎች ጋር ባካሄደው የግማሽ ቀን የምክክር ወቅት ነው ፕሮግራሙ ይፋ የተደረገው።

**https://www.ethiopianreporter.com/133131/**

**3. የሁሉንም የባንክ ካርዶች በመጠቀም ግብይት መፈጸም የሚያስችሉ አሥር ሺሕ የክፍያ ማሽኖች አገር ውስጥ ሊገቡ ነው**

***Reporter: September 8, 2024***

የሁሉንም የባንክ ካርዶች በመጠቀም የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ለመተግበር ያስችላሉ የተባሉ 10,000 የክፍያ ነቁጥ (Pos) ማሽኖችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ስምምነት ተደረገ፡፡

በኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በቴክኖሎጂ የተሳለጠ የክፍያ ሥርዓት ለመዘርጋት የመጀመሪያዎቹን አንድ ሺሕ የክፍያ ማሽኖች ወደ አገር ውስጥ ማስገባቱን፣ የያጉት ፔይ መሥራች አቶ ካሊድ መሐመድ ተናግረዋል፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/133129/**

**4. አዳዲስ ሕጎች የወጡበትና ከፍተኛ ማሻሻያዎች የተደረጉበት የ2016 የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ**

***Reporter;September 8, 2024***

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዙሪያ የፖሊሲ ለውጦችና በርካታ የሚባሉ የሕግ ማሻሻያዎች ተደርገውባቸዋል ተብሎ ሊጠቀሱ ከሚችሉ ወቅቶች ውስጥ የ2016 በጀት ዓመት በቀዳሚነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

በተለይ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች አንፃር ሥር ነቀል የሚባሉ ለውጦች ተካሂደዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በኢትዮጵያ እንግዳ የሚባሉ የኢኮኖሚ የፋይናንስና የኢንቨስትመንት ሕግጋቶች ወጥተዋል፡፡ ከዓመታት እልህ አስጨራሽ ድርድር በኋላ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት አዳዲስ ብድሮችና የገንዘብ ድጋፎች ለማግኘት የተቻለበትም ዓመት ነው፡፡ ይህንንም ተከትሎ የኢትዮጵያ በጀት እንዲጨምር ያስቻለ ሆኗል፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/133183/**

**5. ለሁለት ዓመታት ተቋርጦ የነበረው የሥጋ ኤክስፖርት ተጀመረ**

***Reporter;September 4, 2024***

ለሁለት ዓመት ተቋርጦ የነበረው የከብት ሥጋ ኤክስፖርት መጀመሩን፣ የኢትዮጵያ የሥጋ አምራቾችና ላኪዎች ማኅበር አስታወቀ፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/133103/**

6. **የባቡር ትራንስፖርት የብትን ጭነት ኮንቴይነር ስርአት ተጀመረ**

**ኢ.ዜ.አ ጳጉሜን 4/2016**

**የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት የብትን ጭነት ኮንቴይነር ስርአት ዛሬ በይፋ ተጀምሯል።**

የኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር አክሲዮን ማህበር ዋና ስራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ታከለ ኡማና ከጅቡቲ የንግድና ዱቤሬክተር ጉሌድ አህመድ ዩሱፍ ጋር የኮንቴነሩን ስርዓት በጋራ አስጀምረዋል።

የብትን ጭነት ኮንቴይነር ስርአት ጅማሬ ለባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ወሳኝ እመርታ መሆኑን ኢንጂነር ታከለ ኡማ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት ገልጸዋል።

**https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5130728**

**7. ዲጅታላይዜሽን-የመጪው ጊዜ ብሩህ ተስፋ**

የ13 ወራት ባለጸጋ የሆነችው ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም ለየት ከሚያደርጓት ወራት መካከል አንዷ የጳጉሜ ወር ናት፡፡ ኢትዮጵያውያንም በየዓመቱ አምስት ቀናት እንዲሁም በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ደግሞ ስድስት ቀናት ያሏትን ወርሃ ጳጉሜን በተለያዩ ስያሜዎች ማክበር ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በመሆኑም ጳጉሜ 5 ቀን 2016 ዓ.ም ‹‹የነገ ቀን›› የሚል ስያሜን "የዛሬ ትጋት፣ ለነገ ትሩፋት" በሚል መሪ ሃሳብ እየተከበረ ይገኛል፡፡

**https://press.et/?p=136323**

**8. ኢትዮጵያን ወደፊት ለማሻገር ተስፋ የተጣለበት የማዕድን ዘርፉ**

**Ethiopian press: September 6, 2024**

ኢትዮጵያ ተፈጥሮ የለገሰቻት የማዕድን ሀብት ከፍተኛ ክምችት ያላት ሀገር ብትሆንም ይህ ሀብቷ በተለያዩ ምክንያቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል አልተደረገም። ጥቅም ላይ አለመዋሉ ብቻ ሳይሆን በቅጡ እንዳልተጠናም መረጃዎች ያመላክታሉ። በመሆኑም ቀደም ባሉት ጊዜያት የማዕድን ዘርፉ ትኩረት ተነፍጎት በመቆየቱ የተነሳ እዚህ ግባ የሚባል ሥራ በዘርፍ አልተሰራም። በመሆኑም ሀገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም ሳታገኝ ቆይታለች።

https://press.et/?p=136036

9. **የትራንስፖርት አገልግሎትን የሚያሳልጡ መኪና ማቆሚያዎች በኮሪደር ልማቱ**

**Ethiopian Press:September 7, 2024**

በመዲናዋ የመጀመሪያው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራዎች በስኬት ተጠናቅቀ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ሲሆን፣ የምዕራፍ ሁለት የኮሪደር ልማት ሥራውም ተጀምሯል። የኮሪደር ልማቱ ለከተማዋ ካስገኘላት ጥቅሞች መካከልም ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶች፣ ከዚህ ቀደም ያልነበሩ የብስክሌት መንገዶች፣ የተሸከርካሪ ማቆሚያዎች፣ የመዝናኛ ስፍራዎች፣ ፏፏቴዎች (ፋውንቴኖች) ተጠቃሽ ናቸው። በተለይም የተሸከርካሪ ማቆሚያዎች (ፓርኪንጎች) በስፋት ተገንብተዋል፣ አሁንም እየተገነቡ ነው።

https://press.et/?p=136141

10. **ለምግብ ዋስትና መረጋገጥ የስንዴን እግር እየተከተለ ያለው የሩዝ ምርት**

**Ethiopian Press; September 9, 2024**

የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) እንደሚሉትም፣ በተለይም ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ የሀገሪቱን የሩዝ ፍጆታ ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ለመሸፈን ተችሏል። ኢትዮጵያ ከስንዴና ከቢራ ገብስ ቀጥሎ ከሁለት ዓመታት በኋላ የሩዝ ፍጆታዋን ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት ለመሸፈንና የምግብና ሥነ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየተደረገ ላለው ሀገራዊ ጥረት ወሳኝ ሚና አለው፡፡

**https://press.et/?p=136224**

### 11. አንድ ዓመት ወደ ኋላ – የቱሪዝም ዘርፍ ስኬቶች

**Ethiopian press;September 8, 2024**

የኢትዮጵያ መንግሥት ‹‹የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ናቸው›› በማለት ከለያቸው አምስት ዘርፎች መካከል ቱሪዝምን አንዱ አድርጎታል። በዘርፉም መዋቅራዊ ለውጥ ከማድረግ ጀምሮ በርካታ ማሻሻያዎችን አድርጓል። ይህ ውሳኔ የቱሪዝም ዘርፍን ነፃነት ያወጀና በቀጣይ ለሚካሄዱ የልማት፣ ማስተዋወቅና እንዲሁም የጎብኚዎችን ቁጥር የማሳደግ አቅምን እንደሚጨምር ይጠበቃል።

ኢትዮጵያ የተፈጥሮ፣ የታሪክ፣ የባህል፣ የቅርስ፣ የአርኪዮሎጂና መሰል ሌሎች በርካታ የመስህብ ሀብቶች ባለቤት ነች። በተለይ ጥንታዊ ቅርሶች በስፋት ከሚገኙባቸው ሀገራት ተርታ ትመደባለች። በሰው ልጅ የኪነ ህንፃ ታሪክ ወደር የማይገኝላቸው ሀብቶችን ይዛለች። ከእነዚህ የኪነ ህንፃ ቅርሶች መካከል አብዛኛዎቹ በርካታ ዘመናትን (ምእተ ዓመታትን) የተሻገሩ ናቸው። ከቅርሶቹ ባሻገርም እንክብካቤና ጥበቃ የሚሹ የተፈጥሮ ፓርኮች፣ መልከዓ ምድሮችና የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎች በስፋት ይገኛሉ።

https://press.et/?p=136180

## በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች

### 12.Industrial parks corp prepares to establish subsidiaries ahead of SEZ transition

**Reporter:September 7, 2024**

The Industrial Parks Development Corporation (IPDC) is in the process of establishing a set of subsidiary companies in a bid to better handle the responsibilities of managing more than a dozen industrial parks in the country.

The subsidiaries under formation will be tasked with separately handling logistics, construction, consultancy, manufacturing, and agricultural supply chain services previously under the Corporation.

https://www.thereporterethiopia.com/41799/

### 13.GERD Pivotal in Ensuring Ethiopia's Economic Sovereignty, Says Electric Power CEO

**ENA: September 8/2024**

The Grand Ethiopian Renaissance Dam (GERD) has made a significant contribution in ushering in a paradigm shift to ensure the country's economic sovereignty, remarked Engineer Ashbir Balcha, Chief Executive Officer of Ethiopian Electric Power.

In his message to the people of Ethiopia on his Twitter account, Prime Minister Abiy Ahmed said that the name Ethiopia has always been associated, from time immemorial to date, with honor, glory, and freedom.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5122728

### 14.Ethio-China Investment, Development Cooperation Elevating to New Heights

**ENA: September 8/2024**

Chinese Professor Wang Xingping underscored that the Ethio-China investment and development cooperation have been elevating the bilateral relationship of the two countries to a new heights.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5121022

### 15.Agri Sector Significantly Contributing to Ethiopia's Economic Dev't: Ministry of Agriculture

**ENA:September 8/2024**

The Minister of Agriculture has emphasized the pivotal role of agriculture in fortifying the nation's economic sovereignty, highlighting its substantial contribution to the country's self-sufficiency and economic resilience.

Prime Minister Abiy Ahmed, in his social media post this morning, emphasized that safeguarding sovereignty is paramount to national existence. He elaborated that sovereignty transcends territorial boundaries, encompassing a holistic approach to national autonomy.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5121140

### 16.Ethio-Djibout Railway CEO Confers with Djiboutian Trade, Natural Resource Minister

**ENA: September 9/2024**

The Chief Executive Officer of Ethio-Djibout Railway Company, Takele Umma held talks with Trade and Natural Resources Minister of Djibouti, Yonis Ali Guedi today.

The two sides discussed on issues that would strengthen the economic cooperation between Ethiopia and Djibouti, Ethio-Djibout Railway SC CEO Takele revealed on social media post.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5130663

### 17.Ethiopia's Financial Liberalization Would Bolster Industrial Growth: Economist

**ENA: Septmber 7/2024**

The market-based exchange regime and opening up of the banking industry to foreign banks will immensely contribute to the growth of the industry sector, Economist and policy advisor Costantinos Berhutesfa said.

Ethiopia has undertaken significant economic reforms to open up the economy, including the liberalization of the telecom sector, opening up of the financial sector, the liberalization of trade and the logistics sector for foreign investors, among others.

Ethiopia has undertaken significant economic reforms to open up the economy, including the liberalization of the telecom sector, opening up of the financial sector, the liberalization of trade and the logistics sector for foreign investors, among others.

Ethiopia has undertaken significant economic reforms to open up the economy, including the liberalization of the telecom sector, opening up of the financial sector, the liberalization of trade and the logistics sector for foreign investors, among others.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5118398